# Learning by Ear 2013

"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ "መዘዙን መቀበል"

EPISODE 19: ነባር እና አዲስ ጓደኞች

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**<u>INTRO/OUTRO:</u> NARRATOR**

**<u>SCENE 1: ሰብለ ASKS በለጠ ABOUT DAN</u>**

- **ሰብለ (F, 50)**
- **በለጠ (M, 16)**

**<u>SCENE 2: ምኞቴ RESTRICTS ትዕግስት'S MOVEMENTS</u>**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምኞቴ (M, 35)**

**<u>SCENE 3: አልማዝ AND ምህረት RECONCILE</u>**

- **ምህረት (F, 15)**
- **አልማዝ (F, 16)**
- **እየሩስ (F, 15)**
- **3 – 5 STUDENTS (M/F)**

**<u>SCENE 4: ምህረት LOOKS FOR ትዕግስት</u>**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 15)**

- ምኞቴ **(M, 35)**

## **INTRO**

## 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ስር "መዘዙን መቀበል"በተሰኘዉ ሁለተኛው ዙር ድራማ ላይ እንገኛለን። በእዚህ ትምህርታዊ ተከታታይ የራድዮ ድራማ ቦንጎ አካዳሚ አዳሪ ትምህርት ቤት የገቡ አፍሪቃውያን ታዳጊ ልጆችን የየዕለት ህይወት እየተከታተልን እንገኛለን፡፡ እስኪ እስከአሁን ምን እንደተከናወነ እንመልከት…**

**ትዕግስት ብዙ ዓመት ወደ ሚበልጣት የወንድ ጓደኛዋ ምኞቴ ቤትጠቅልላ| ገብታለች፡፡ እንደ አስደሳች ነገር የጀመረችው ህይወት በድንገት ጓደኛዋ ምኞቴ ተለዉጦ በመጥፎ ሁኔታ ሲያስጨንቃት አስደሳቹ ነገርዋ ሁሉ ወደ ቅዠትነት ተቀይሯል፡፡**

## *2.* EPISODE 16, LINES 143 – 145:

> **<u>ምኞቴ</u>: ነይ እንጂ ትዕግስት፡፡ አንድ ላይ እየኖርን ነን፡፡ ያ ማለት ደግሞ እንደ ባል እና ሚስት ነን ማለት ነው፡፡** *(…)*
>
> **<u>ትዕግስት</u>: ምኞቴ፣ እባክህን፡፡.** *(…)*
>
> **<u>ምኞቴ</u>:** *(…)***ሚስቴ እንደመሆንሽ እኔን መታዘዝ አለብሽ፡፡** ***(roughly)*** **ነይ እዚህ ጋር!**

## 3. NARRATOR:

**ይህ በእንዲህ እንዳለ የትዕግስት ጓደኛ ምህረት በማርገዟ ምክንያት ለብዙ ወራት ከትምህርት ቤት ታግዳ ነበር፡፡ ምህረት ወደ ትምህርት ቤት በተመለሰች የመጀመሪያው ዕለት ከጎረቤት ሀገር ላቦሪያ በልውውጥ መረሃ-ግብር ተማሪነት የመጣችዉ አልማዝን አገኝታታለች፡፡ ግን አልማዝ ከምህረት ጋር ጓደኛ መሆን የፈለገች አይመስልም፡፡**

## 4. EPISODE 18, LINES 81 – 82:

<u>አልማዝ</u>: የወንድ ጓደኛዬን ከእኔ ወሰድሽ፣ እንዲባረር አደረገሽው በዝያ ላይ አሁን ልጁን ሆድሽ ውስጥ ተሸክመሻል! ታስጠይኛለሽ፣ ምህረት!

<u>ምህረት</u>: ግን እ…እ… አላወቅኩም… እባክሽን ባላወቅሁት ነገር አትጥዩኝ!

## 5. NARRATOR:

ሁለቱ እንዲያ የሚያወሩለት ልጅ ልክ  እንደ አልማዝ ሁሉ ከጎረቤት አገር ላቦሪያ የመጣው ዳንኤል ካሳሁን ነው። ዳንኤል ከትምህርት ቤት በመባረሩ እና እስካሁንም ወደ ት/ቤት ባለመመለሱ  ሁለቱ ሴቶች መገናኘታቸውን አያውቅም። ዛሬ በሚቀርበዉ “ነባር እና አዲስ ጓደኞች” በተሰኘው  አስራ ዘጠነኛው ክፍል ድራማ የታሪኩን ፍሰት አብረንእንከታተል። ድራማዉ የሚጀምረዉ በቦንጎ አካዳሚ በርዕሰ መምህርቷ ቢሮ ውስጥ ሳለ ነዉ ,,,,,

## <u>SCENE 1: ሰብለ ASKS በለጠ ABOUT DAN</u>

## 6. ATMO: ሰብለ’S OFFICE AT BREAK TIME

**7.** ሰብለ: በለጠ ስለ ጓደኛህ ዳንኤል በቅርቡ የሰማኸው ነገር አለ?

**8.** በለጠ: ምንም አልሰማሁም፣ ርዕሰ መምህርት ሰብለ

**9.** ሰብለ: ዳንኤል ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ የሚያሳስብ ደብዳቤ እዚሀ ኪሲምባ ወስጥ ለሚኖረው አጎቱ  ልከን ነበር። ደብዳቤዉን ከላክን ጥቂቲ ጊዜያት ቢያልፍም መልስ ግን አላገኘንም። ዳንኤል ወደ ላቦሪያ ተመልሶ እንደሆነ የምታውቀው ነገር አለለህ?

**10.** በለጠ: አንድ ጊዜ ሳናግረው በጦርነቱ የተነሳ ወደ ላቦሪያ መመለስ እንደማይፈልግ ነግሮኝ ነበር።

**11.** ሰብለ: ውጊያው ግን ጦር ሰራዊቱ ስልጣኑን ከጨበጠ በኋላ የቀዘቀዘ ይመስልል፡፡

**12.** በለጠ: መምህርት በእውነቱ የማዉቀዉ ነገር የለም፤

**13.** ሰብለ: ትዕግስትስ? ስንት ቀን ከትምህርት ቤት ቀረች?

**14.** በለጠ: ሁለት ሳምንታት ገደማ ነው፤ መምህርት .

**15.** ሰብለ: ምን እንደሆነች የሚያውቅ ሰው አለ?

**16.** በለጠ: **(hesitates)** የሆነ የሚናፈስ ወሬ አለ,,,,እእ,,,

**17.** ሰብለ: ምን እየተባለ?

**18.** በለጠ: አሚታል...፣ ይባላል፡፡ እትዬ ሰብለ

**19.** ሰብለ: በለጠ! ወደ እኔ ተመልከት፡፡ እየነገርከኝ ያለው እውነት ነው?

**20.** በለጠ: የሰማሁት ያንን ነው መምህርት

***KW BEGIN***

**21.** ሰብለ: እና እየዋሸኸኝ አይደለም፣ አይደል?

**22.** በለጠ: አይደለም እትዬ ሠብለ!

**23.** ሰብለ: እንዳትረሳ የክፍል አለቃ ነህ፡፡ የምትዋሸኝ ከሆነ ምን ሊከሰት እንደሚችል ታውቃለህ፡፡.

**24.** በለጠ: አውቃለሁ መምህርት.

***KW END***

**25.** ሰብለ: እሺ፡፡ ስለ መረጃህ አመሰግናለሁ፡፡ አሁን ለእረፍት መውጣት ትችላለህ ግን እያንዳንዷን ነገር ለመስማት ጆሮዎችህን እና አይኖችህን ከፍተህ ተከታተል እና ያገኘኸውን ነገር ወዲያውኑ እንድታሳውቀኝ እፈልጋለሁ፡፡ ግልጽ ነው?

**26.** በለጠ: አዎ፣ አትዬ ሰብለ፤

**27.** ሰብለ: እሺ፡፡ ስትወጣ በሩን ዝጋው፡፡.

**28. SFX: FOOTSTEPS**

**29. SFX: DOOR CLOSED**

**30.** ሰብለ: **(To herself)** እዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ ነው? አይን ከሚያየው የበለጠ ብዙ ነገር …

**31. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: ምኞቴ RESTRICTS ትዕግስት MOVEMENTS**

**32. ATMO: AT ምኞቴ'S, DAYTIME**

**33. SFX: BOOKS PACKED INTO BAG**

**34.** ምኞቴ: ምን እያደረግሽ ነው ትዕግስት?

**35.** ትዕግስት: እቃዬን እየሰበሰብኩ ነው፡፡ ሁለት ሳምንታት ከትምህርት ቤት ቀረሁ። እዚህ እስረኛ እንደ ሚጠብቅ ከአጠገቤ ተጎልተህ መመልከቱ ሰልችቶኛል!

***KW BEGIN***

**36.** ምኞቴ: **(menacingly)** ትዕግስት፣ አንቺ እኮ ሚስቴ ነሽ! እኔ ካልፈቀድኩ በስተቀር ይህንን ቤት ለቅቀሽ መሄድ አትችይም!

**37.** ትዕግስት: ሚስትህ አይደለሁም! እንኳን እንዲህ አድርገኸኝ ቀርቶ መቼም ቢሆን ሚስትህ አልሆንም። ምን እንዳደረግኸኝ ታውቃለህ! እሄዳለሁ!

***KW END***

**38.** ምኞቴ: አይሆንም። እዚሁ ትቀመጫለሽ!

**39.** ትዕግስት: ለምን? ከእኔ የምትፈልገው ምንድን ነው?

**40.** ምኞቴ: አውቃለሁ። ከዚህ ክፍል በወጣሽበት ደቂቃ ልጄን ትጎጂዋለሽ።

**41.** ትዕግስት: የምን ልጅ? ይሄ  እብደት ነው! አስገድደኸኝ ያለ መከላከያ ስለደፈርከን ብቻ አርግዣለሁ ማለት አይደለም!

***KW BEGIN***

**42.** ምኞቴ: አትከራከሪኝ። እዚህ ትቆያለሽ ትቆያለሽ ነው በቃ!

**43.** ትዕግስት: **(still strong)** እዚህ ለዘለዓለም ዘግተህብኝ ልቀመጥ አልችልም። እናቴ ትፈልገኛለች።

**44.** ምኞቴ: **(laughs)** እናትሽ ገደል ብትገቢም ጉዳይዋ አይደለም። ከእኔ ጋር ከመጣሽበት ጊዜ አንስቶ አንድ ቀን እንኳ ደውላልሽ ታውቃለች?

**45.** ትዕግስት: **(cries)**

**46.** ምኞቴ: አንቺን ብሆን ኖሮ አፌን ዘግቼ እናትነት መሆኑ ላይ አተኩር ነበር።.

**47.** ትዕግስት: **(cries)** ግን ምኞቴ፣ ትምህርት ቤት መሄድ እንደምችል ተስማምተን ነበር።

**48.** ምኞቴ: ልክ ነው፣ ግን ሀሳቤን ቀይሬያለሁ!

**49.** ትዕግስት: ግን…

***KW END***

**50. SFX: TABLE BANGED**

**51.** ምኞቴ: **(angrily)** ክርክርሽን አቁሚነዉ የምለዉ!

**52.** ትዕግስት: **(scared)** እሺ፣ እሺ! እንደገና አትምታኝ እባክህን። እቀመጣለሁ፡ እቀመጣለሁ፡ እባክህን አትምታኝ… **(whimpers)**

**MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 3: አልማዝ AND ምህረት RECONCILE

**53. SFX: BELL RINGS**

**54. ATMO: BONGO ACADEMY, INSIDE CLASSROOM AFTER SCHOOL**

**55. SFX: DOOR OPENS**

**56. SFX: STUDENTS DISPERSE (call to each other: "**ቻዎ እስክነገ፤ ባይ **etc…)**

**57.** ምህረት: **(shyly)** ቻዎ፣ አልማዝ፤ ነገ እንገናኝ።.

**58.** አልማዝ: **(annoyed)** እሺ ምህረት ነገ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ የመጀመሪያ የምክክር ጊዜያችን ነው፡ እንዳትቀሪ።.

**59.** ምህረት: **(to herself, sadly)** ጥሩ፤ እስኪ.ደርስ ቸኩያለሁ።.

**60.** አልማዝ: ምን አልሽ?

**61.** ምህረት: እ…እ…ምንም። እመጣለሁ

**62.** እየሩስ: **(from a distance)** ሄይ፣ እዛ ጋር ተመልከች! ሁለቱ የዳንኤል ካሳሁን ሚስቶች አሪፍ ውይይት ይዘዋል።.

**63. STUDENTS LAUGH**

**64.** ምህረት/አልማዝ: **(shout at the same time)** አፍሽን ዝጊ እየሩስ! ለምን አትተዊንም!

**65.** እየሩስ: **(impressed)** ኧረ፣ እሺ፣ እሺ…

**66.** ምህረት/አልማዝ: **(laugh)**

**67. PAUSE**

**68.** አልማዝ: ይህ ማለት ሁሉም ሰው ስለ እኛ እና ዳንኤል ያወቀ ይመስላል?

**69.** ምህረት: ተያት ባክሽ፣ እየሩስን እርሻት። ሁሌ ታናድደኛለች! እንዲህ ለምን እንደምትጠላኝም አልገባኝም።.

**70.** አልማዝ: **(thoughtful)** ግን ልክ ትመስላለች፣ አይደለችም?

**71.** ምህረት: **(disappointed)** ጥሩ፣ እንደእዛ ካልሽሽ።.

**72.** አልማዝ: አይደለም አይደለም፤ በእዛ መልኩማለቴ አይደለም። ግን …ሁለታችንም የዳንኤል ካሳሁን ሚስቶች መባላችንን ነው። ይሄን ነበር ለማለት የፈለግሁት፡

**73.** ምህረት: ነው?

**74.** አልማዝ: እውነቱን ለመናገር ዳንኤል ሁለታችንንም ክዶናል፣ አይደለም እንዴ **(takes a deep breath)** ምህረት ስሚኝ፤ በጣም አዝናለሁ። በአንቺ ላይ እንደዛ ክፉ በመሆኔ አዝናለሁ። ቀንቼ ነው።.

**75.** ምህረት: ወይኔ አልማዝ-ምንም አይደለም። እውነት ለመናገር ተረድቼሻለሁ። የወንድ ጓደኛሽ እንዳታለለሽ ስትረጂ ምን እንደሚሰማሽ ይገባኛል።

**76.** ምህረት/አልማዝ: **(laugh)**

**77.** አልማዝ: ጠላቴ አይደለሽም እኔም ጠላትሽ አይደለሁም።.

**78.** ምህረት: በእርግጥ አይደለንም። ነይ እባክሽ አሁን ተነስተን እንሂድ…

**79. SFX: FOOTSTEPS OF TWO PEOPLE IN CORRIDOR**

**80.** አልማዝ: እና…አንቺ እና ዳንኤል እንዴት ተለያያችሁ?

***KW BEGIN***

**81.** ምህረት: አላውቅም…ይቅርታ፣ግን በእዚህ ጉዳይ ካንቺ ጋር ለመወያየት ጥሩ ስሜት ስለሌለኝ ብንተወው ይሻላል …

**82.** አልማዝ: ምህረት፣ ጠላቶች እንዳልሆንን ነግሬሻለሁ። አንቺ ላይ ይሄንእንዴት እንዳደረገ ማወቅ እፈልጋለሁ። ለሁለታችንም ስል ነው።.

***KW END***

**83.** ምህረት: **(sighs)** ጥሩ …እዚህ ቦንጎ አካዳሚ መጀመሪያ ከገባንነበት ዕለት አንስቶ ሲከታተለኝ ነበር። መጀመሪያ ላይ እምቢ ብለውም አልተው አለኝ። ያፈቀረኝም መሰለኝ። እርሱም አፍቅሬሻለሁ አለኝ። የሴት ጓደኛ እንደነበረችው ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም…ወይአምላኬ! ግልጽና የዋህ ነበርኩ!

**84.** አልማዝ: የሚገርምሽ ይህንን ሁሉ ጊዜ ስጠብቀው፣ ደብዳቤ ስጽፍለት እና ስደውልለት…ነበር ! ሊያናግረኝ ባይፈልግ አያስገርምም።

**85. SFX: MAIN DOOR OPENING AND CLOSING, TWO PEOPLE GOING THROUGH**

**86. SFX: ATMO CHANGES: EXTERIOR, BONGO ACADEMY, AFTER SCHOOL**

**87. SFX: FOOTSTEPS TWO PEOPLE OUTSIDE**

**88.** ምህረት: አዝናለሁ፣ አልማዝ። አውቄ ቢሆን ኖሮ በፍጹም አልጀምረዉም ነበር።
ታውቂያለሽ ትንሽም ቢሆን ለዚህ ያበቃችኝ ትዕግስት ናት። **(sarcastic)**
ዳንኤልን እንድይዘዉ እና “እውነተኛ ሴት” እንዲያደርገኝ አሳመነች …

**89.** አልማዝ: ትዕግስት ማን ናት?

**90. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**91.** ምህረት: **(taken aback**) ትዕግስት? ትዕግስትን ታውቂያታለሽ! የእኛ ክፍል ልጅ
ናት…ምን ያህል ጊዜ ሆነሽ ግን?

**92.** አልማዝ: ሁለት ሳምንታት።

**93.** ምህረት: እንዴት እስከ አሁን ትዕግስትን አላገኘሻትም?

**94.** አልማዝ: ምንአልባት ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮ ትምህርት ቤት አልገባች ይሆናል።.

**95.** ምህረት: **(worried)** ህምም! ትዕግስት እንደሱ አይነት ተማሪ አይደለችም!
ከትምህርት ቤት የምትቀረው ጥቂት ቀናት ሊሆን ይችላል! ሳምንቱን ሙሉ
ትምህርት ቤት የመቅረት ባህሪ የላትም።.

**96.** አልማዝ: ምን አልባት ስለእሷ ማጣራት ይኖርብሻል መሰለኝ።

***KW BEGIN***

**97.** ምህረት: ህምም…አሁን እንኳ የልብ ጓደኛሞች አይደለንም…ግን እስኪ
እፈልጋታለሁ። ወደ ቤት ስሄድ ቤትዋ በመንገዴ አቅጣጫ ስለሆነ፤ ሰፈሯ
ድረስ እሄድ እና ምን እንዳጋጠማት አጣራለሁ።

**98.** አልማዝ: እሺ። ነገ እንገናኝ ምህረት።

**99.** ምህረት: በይ ቻዎ አልማዝ

***KW END***

**100. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ምህረት LOOKS FOR ትዕግስት</u>**

**101. SFX: KNOCKING ON DOOR**

**102. SILENCE**

**103.** ምህረት: እዚህ ቤት? ሰው አለ? …ትዕግስት?

**104. SFX: KNOCKING AGAIN**

**105.** ምህረት: **(to herself)** እንዴ፣ ቤት ውስጥ ማንም የለም። የትዕግስት ጎረቤት ግን ምኞቴ መኖሪያ አካባቢ እንድፈልጋት ነግራኛለች። ከዚህ ሌላ የት ልትሆን ትችላለች ታዲያ?

**106.** ትዕግስት: **(from inside)** አቤት? ማን ነው?

**107.** ምህረት: ትዕግስት? አንቺ ነሽ?

**108.** ትዕግስት: **(relieved)** አዎ! ምህረት ነሽ? ወይ፣ አምላኬ አመሰግንሻለሁ! እባክሽን፣ እባክሽን ከዚህ አውጪኝ!

**109. SFX:** ምህረት **TRIES TO OPEN THE DOOR, LOCKED DOOR RATTLES**

**110.** ምህረት: ትዕግስት፣ ብቻሽን ነሽ? በሩን የቆለፈው ማን ነው? ምን ሆነሽ ነው፤_ ምንድን ነዉ ነገሩ?

**111.** ትዕግስት: ምኞቴ አብዷል! እዚህ ቆልፎ አስቀምጦኛል! እንድወጣ አይፈልግም።

**112. SFX: SOUND OF DOOR/PADLOCK AS SHE TRIES TO OPEN IT**

***KW BEGIN***

**113.** ምህረት: የሚገርም ነው፣ ትዕግስት! ለስንት ጊዜ ነዉ እንዲህ የዘጋብሽ?

**114.** ትዕግስት: ሁለት ሳምንቴ ነዉ!

**115.** ምህረት**:** ለምን ርዳታ አልጠራሽም?

**116.** ትዕግስት: ያ እብድሰውዬ ስልኬን ወሰደው፡፡ ምህረት፣ እባክሽን እርጂኝ!

***KW END***

**117.** ምኞቴ**:** **(from a distance, drunk, to himself)** አትጨነቂ እማ
ከመሞትሽ በፊት የልጅ ልጅ እሰጥሻለሁ…

**118.** ምህረት: ወይ አምላኬ! እሱ ነው! እየመጣ ነው!

**119.** ትዕግስት: **(urgently)** ፍጠኚ! ሰውዬው እብድ ነው፡፡ እሱ ጋር ካየሽ ምን ሊከሰት
እንደሚችል ማወቅ አይቻልም፡፡ ሄደሽ የሆኑ ሰዎችን ጥሪ!

**120.** ምህረት: **(whispers loudly)** አትጨነቂ! አሁኑኑ እመለሳለሁ!

**121. SFX: FOOTSTEPS AS SHE RUNS**

**122.** ምህረት: **(to herself while she runs and hides)** ወይ አምላኬ፣
እንዳላየኝ ተስፋ አደርጋለሁ!

**123. SFX: MAN’S HEAVY FOOTSTEPS (HEARD FROM A DISTANCE)**

**124. SFX: KEY TURNS IN PADLOCK (HEARD FROM A DISTANCE)**

**125. SFX: DOOR OPENS (IN THE DISTANCE)**

**126.** ምኞቴ**:** **(drunk, at a distance)** እሺ ትዕግስት፡፡ መጥቻለሁ!

## 127. OUTRO – NARRATOR:

**ምህረት ጓደኛዋን ትዕግስትን መርዳት ትችል ይሆን? በምህረት እና በአልማዝ መካከል የተፈጠረው አዲስ ጓደኝነትስ ይዘልቃል? ያደመጣችሁት "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ "መዘዙን መቀበል" የተሰኘዉ ሁለተኛው ዙር ድራማ ክፍል አስራ ዘጠኝን ነበር። የድራማውን ያለፉትን ክፍሎች ማድመጥ አልያም ድራማዉን በግል ማህደር መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኛሉ። በፌስቡክ አድራሻችን ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል እስክንገናኝ በእዚሁ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።**